# Environmental Justice Council
# የ 2022 እና የመጀመሪያው ሩብ አመት የ 2023 ስብሰባ መርሃ ግብር

በ Open Public Meetings Act (ክፍት ህዝባዊ ስብሰባዎች ህግ) (አንቀጽ 42.30 Revised Code of Washington (RCW፣ የተከለሰው የዋሺንግተን ኮድ)) እና በ Administrative Procedure Act (የአስተዳደራዊ አሰራር ህግ) (አንቀጽ 34.05 RCW) መሰረት፣ ከዚህ የሚከተለው በ 2022 እና በ 2023 የመጀመሪያ ሩብ አመት የ Washington State Environmental Justice Council (የዋሽንግተን ስቴት የአካባቢ ፍትህ ምክር ቤት) (ምክር ቤት) መደበኛ ስብሰባዎች መርሃ ግብር ነው። የምክር ቤቱ ስብሰባዎች ለህዝብ ክፍት ናቸው። ህብረተሰቡ ስብሰባውን እና የቋንቋ ፍትህን ማግኘታቸው ምክር ቤቱ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ነገሮች ናቸው። የምክር ቤት ስብሰባዎችን እና የቁሳቁሶችን ተደራሽነት ለማሻሻል የህዝቡ አባላት የቋንቋ አስተርጓሚዎችን በስብሰባዎች፣ የተተረጎሙ የስብሰባ ቁሳቁሶች፣ ወይም ማሻሻያዎች ለመጠየቅ ከሰራተኞች ጋር (ከዚህ በታች ይመልከቱ) መነጋገር ይችላሉ።

ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ስብሰባዎች፣ አጀንዳዎች በቅድሚያ በ listserv በኩል እና በምክር ቤቱ ድህረ ገጽ (ከዚህ በታች ይመልከቱ) መገኘት እንዲችሉ ተደርገዋል። አጀንዳው ወቅቱን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ እያንዳንዱ ሙከራ ይደረጋል። ይሁን እንጂ፣ በስብሰባው ላይ ምክር ቤቱ አጀንዳዎችን የመቀየር ወይም የማሻሻል መብቱ የተጠበቀ ነው።

| የስብሰባ ቀን | ቦታ |
| --- | --- |
| የተረጋገጠ፡-<br>ሰኞ<br>ኤፕሪል 4፣ 2022<br>2:00pm-6:30pm | በቨርቹዋል ብቻ<br>የዙም ስብሰባ ይቀላቀሉ፡-<br>https://us02web.zoom.us/j/85252692400<br>(በእንግሊዘኛ)<br>ወይም በ ስልክ ይቀላቀሉ፡- +1 253 215 8782<br>የስብሰባ መታወቂያ፡- 852 5269 2400 |

| | |
|---|---|
| የተረጋገጠ፦<br>ረቡዕ<br>ሜይ 25፣ 2022<br>2:00pm-6:30pm<br>(የስብሰባ ቀን ተረጋግጧል) | በቨርቹዋል ብቻ |
| የተረጋገጠ፦<br>ረቡዕ<br>ጁን 22፣ 2022<br>10:00am-3:00pm<br>(የስብሰባ ቀን ተረጋግጧል) | በቨርቹዋል ብቻ |
| የቀረበው፦<br>ቅዳሜ<br>ኦገስት 27፣ 2022<br>10:00am-3:00pm | ወደፊት የሚወሰን ይሆናል (ምናልባት በአካል በቨርቹዋል የመቀላቀል አማራጭ ጋር) |
| የቀረበው፦<br>ሐሙስ<br>ኦክቶበር 27፣ 2022<br>3:00pm-7:30pm | በቨርቹዋል ብቻ |
| የቀረበው፦<br>ማክሰኞ<br>ዲሴምበር 13፣ 2022<br>2:00pm-6:30pm | በቨርቹዋል ብቻ |
| የቀረበው፦<br>ማክሰኞ<br>ፌብሩዋሪ 28፣ 2023<br>3:00pm-7:30pm | ወደፊት የሚወሰን ይሆናል |
| የቀረበው፦<br>ረቡዕ<br>ኤፕሪል 26፣ 2023<br>2:30pm-7:00pm | ወደፊት የሚወሰን ይሆናል |

ሰአት እና ቦታዎች እንደ አስፈላጊነቱ የሚለወጡ ይሆናል። ወቅታዊ የሆነውን መረጃ ለማግኘት

Environmental Justice Council | WaPortal.org (በእንግሊዘኛ) ይመልከቱ። የምክር ቤት

ሰራተኞቻችንን በ envjustice@ejc.wa.gov ወይም በ 360-584-4398 ያግኙ።

| የስብሰባ አጀንዳ፣ ቁሳቁሶች፣ እና ማስታወሻዎች |
| --- |
| አጀንዳ<br>የስብሰባ ቅጂ<br>የስብሰባውን ቁሳቁሶች እና ማስታወሻዎችን ለመጠየቅ እባክዎ በማንኛውም ቋንቋ በ envjustice@doh.wa.gov ኢሜይል ይላኩ ወይም በ 360-584-4398 ይደውሉ (የስልክ ትርጉም ማግኘት ይችላሉ) |

ለመጨረሻ ጊዜ የዘመነው በ 04/26/2022

የመግቢያ ገጽ
ብዙውን ጊዜ በስቴቱ ውስጥ በጣም በብዛት እና በተደጋጋሚ በአካባቢ ጤና አደጋዎች ተጽዕኖ የሚያድርባቸው ማህበረሰቦች የአካባቢ ኢ-ፍትሃዊነትን ለመቅረፍ ግልጽ እና ውጤታማ የሚባሉ ዘዴዎች የሏቸውም። ምክር ቤቱ ተመጣጣኝ ያልሆነ ተጽዕኖ ስለሚደርስባቸው ማህበረሰቦች ለስቴቱ የአካባቢ ፍትህ ጥረቶች ለማሳወቅ ድምጽ ሊያመጣ የሚችል መድረክ ያቀርባል።

**አላማ እና ሃላፊነቶች**

የ Environmental Justice Council (የአካባቢ ፍትህ ምክር ቤት) አላማ የስቴት ኤጀንሲዎችን፣ የአካባቢ ፍትህን በኤጀንሲው ተግባራት ውስጥ ስለማካተት ማማከር ነው። የተካተቱ የተለዩ የምክር ቤት ግዴታዎች እነዚህን ለማድረግ ነው፡-

- እንደ የአካባቢ ፍትህ ግምገማ፣ የማህበረሰብ እቅዶች፣ እና ዘዴያዊ እቅዶች ያሉ የአካባቢ ፍትህ መስፈርቶችን በመተግበር ለስቴቱ ምክክሮችን ያቅርቡ።
- ሃላፊነትን ከልክ በላይ የተሸከሙ ማህበረሰቦችን በመለየት የአካባቢ ጤና ልዩነቶች ካርታ ጥቅም ላይ መመሪያ ያዘጋጁ።
- በዋሽንግተን ውስጥ የጤና ፍትሃዊነትን በመጨመር እና የአካባቢ ፍትህን በማረጋገጥ እድገትን ይከታተሉ።
- ከካርቦን ገቢዎች የገንዘብ ድጋፍ የተደረገላቸውን ፕሮግራሞች ጨምሮ በአየር ንብረት ፕሮግራሞች ልማት እና ትግበራ ላይ ምክሮችን ይስጡ።
- የአካባቢ ፍትህ ጉዳዮች እና ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ መድረክ በመሆን ያገልግሉ።
- የአካባቢ ፍትህን በሚያፋጥኑ ድርጊቶች ላይ ለገዢው እና ለህግ አውጪው ምክሮችን ያቅርቡ።

የአካባቢ ፍትህ ላይ በቀጥታ ተጽዕኖ የሚያመጡ ፖሊሲዎችን እና ፕሮግራሞችን የሚያዘጋጁ ሰባት የዋሽንግተን ስቴት ኤጀንሲዎች የ Healthy Environment for All Act (HEAL Act፣ የጤናማ አካባቢ ለሁሉም ህግ) ን ማክበር አለባቸው፡-

- Department of Agriculture (የግብርና መምሪያ)
- Department of Commerce (የንግድ መምሪያ)
- Department of Ecology (የስነ-ምህዳር መምሪያ)
- Department of Health (የጤና መምሪያ)
- Department of Natural Resources (የተፈጥሮ ሃብቶች መምሪያ)
- Department of Transportation (የመጓጓዣ መምሪያ)
- Puget Sound Partnership (የፑጌት ሳውንድ አጋርነት)

የሌሎች ስቴት ኤጀንሲዎች የ HEAL Act ን በፈቃደኝነት ማክበር ይችላሉ።

## ስልጣን

Chapter 70A.02 RCW (አንቀጽ 70A.02 Revised Code of Washington (RCW፣ የተከለሰው የዋሺንግተን ኮድ)) (በእንግሊዘኛ) በሜይ 17፣ 2021 በህግ ተፈርሟል። Department of Health እንዲሰበስብ እና Environmental Justice Council እንዲሰራ ይመራል። ህጉ የምክር ቤቱን አባልነት፣ ግዴታዎች፣ እና ለህግ አውጪው አካል ሪፖርት የማድረጊያ መስፈርቶችን ይጠቅሳል።

## አባልነት

ምክር ቤቱ በአስተዳዳሪው የተሾሙ 16 አባላት (በእንግሊዘኛ) ን ይይዛል። የምክር ቤት አባልነት የማህበረሰብ ተወካዮችን፣ የወጣት ማህበረሰብ ተወካይን፣ የአካባቢ ፍትህ ባለሙያዎችን፣ የጎሳዎችን፣ የስራ እና የቢዝነስ መቀመጫዎችን ያካትታል። በምክር ቤቱ ውስጥ ለማገልገል ለመሾም ታሳቢነት ውስጥ እንዲገቡ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች በ ገዢው ቦርዶች እና የኮሚሽኖች ድህረ ገጽ (በእንግሊዘኛ) ማመልከት ይችላሉ። ከእያንዳንዱ የተሸፈነ ኤጀንሲ አንድ የህግ አስፈጻሚነት ደረጃ ያለው ሰው ለምክር ቤቱ ድምጽ-የማይሰጥ ግንኙነት በመሆን ያገለግላል።

## የተያያዙ መርጃዎች

የአካባቢ ፍትህ (በእንግሊዘኛ)

የአካባቢ ፍትህ ስራ ሃይል (በእንግሊዘኛ)

Climate Commitment Act (የአየር ሁኔታ ቁርጠኝነት ህግ) (በእንግሊዘኛ)

የአካባቢ ፍትህ እውነታ ወረቀት (PDF) (በእንግሊዘኛ)

የእውነታ ወረቀት በስፓኒሽ (PDF) | የእውነታ ወረቀት በቪትናምኛ (PDF) | የእውነታ ወረቀት በራሽያኛ (PDF)

## ያግኙን

envjustice@doh.wa.gov, 360-584-4398

ለ Environmental Justice Council የኢሜይል አዲስ መረጃዎች ሰብስክራይብ ያድርጉ (በእንግሊዘኛ)

# የ Environmental Justice Council አባላት

ስም፦ Nichole Banegas

መቀመጫ፦ ሽፋን ባለው ኤጀንሲ የሚተዳደር እና መደበኛ የንግድ ሁኔታዎቹ ቢያንስ አንድ ሌላ ሽፋን ያለው ኤጀንሲ በሚወስደው እርምጃ ጉልህ ተጽዕኖ የሚያድርበት የቢዝነስ ተወካይ

የኢሜይል አድራሻ፦

የስራ ዘመኑ የጀመረው፦ 01/06/2022

የስራ ዘመኑ የሚያበቃው፦ 07/25/2023

ግለ-ታሪክ፦

ስም፦ Maria Batayola

መቀመጫ፦ የማህበረሰብ ተወካይ

የኢሜይል አድራሻ፦

የስራ ዘመኑ የጀመረው፦ 01/06/2022

የስራ ዘመኑ የሚያበቃው፦ 07/25/2025

ግለ-ታሪክ፦

ስም፦ Maria Blancas

መቀመጫ፦ የማህበረሰብ ተወካይ

የኢሜይል አድራሻ፦

የስራ ዘመኑ የጀመረው፦ 01/06/2022

የስራ ዘመኑ የሚያበቃው፦ 07/25/2025

ግለ-ታሪክ፦ ወ/ሪት Blancas በቅርቡ ከ University of Washington የ Community-Oriented Public Health Practice (የማህበረሰብ-ተኮር የህዝብ ጤና ልምምድ) ፕሮግራም የ MPH ዲግሪዋን አጠናቃለች። የ Outreach (ተደራሽ) ቡድን አባል እንደመሆኗ፣ በማዕከሉ የወተት ተዋጽዖ ሰራተኛ እና የቤተሰብ ፕሮጀክቶች ላይ የማህበረሰብ ተሳትፎ ለማቅረብ እገዛ እያደረገች ነው። የወ/ሪት Blancas የቀድሞ ልምድ ከ Promotores de Salud እና ከእርሻ ሰራተኞች ጋር የጤና ፍትሃዊነትን ለማምጣት አብሮ መስራትን ያካትታል። የታታሪ ገበሬ ሰራተኛ ወላጆች ልጅ እንደመሆኗ፣ ወ/ሪት Blancas የእርሻ ሰራተኞች እና ቤተሰቦቻቸውን ደህና እና ጤናማ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እየሰራች ነው።

ስም፡- የተከበሩ Patrick DePoe

መቀመጫ፡- ከዌስተርን ዋሽንግተን የጎሳ ማህበረሰብ ተወካይ አባል

የኢሜይል አድራሻ፡-

የስራ ዘመኑ የጀመረው፡- 02/11/2022

የስራ ዘመኑ የሚያበቃው፡- 07/25/2025

ግለ-ታሪክ፡-

ስም፡- የተከበሩ Jarred-Michael Erickson

መቀመጫ፡- ከኢስተርን ዋሽንግተን የጎሳ ማህበረሰብ ተወካይ አባል

የኢሜይል አድራሻ፡-

የስራ ዘመኑ የጀመረው፡- 02/11/2022

የስራ ዘመኑ የሚያበቃው፡- 07/25/2023

ግለ-ታሪክ፡-

ስም፡- Running-Grass

መቀመጫ፡- የአካባቢ ፍትህ ባለሙያ ሆኖ የሚያገለግል የአካባቢ ፍትህ ባለሙያ ወይም የአካዳሚ ሰራተኛ

የኢሜይል አድራሻ፡-

የስራ ዘመኑ የጀመረው፡- 01/06/2022

የስራ ዘመኑ የሚያበቃው፡- 07/25/2023

ግለ-ታሪክ፡- Running-Grass ለረጅም ጊዜ የአካባቢ እና የዘር ፍትህ አክቲቪስት እና አስተማሪ ነው። የአካባቢ አክቲቪዝም እንቅስቃሴው የጀመረው ከመጀመሪያው የመሬት ቀን በፊት በ 1970፣ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪ እያለ በቤቱ አቅራቢያ ባሉ ወንዞች እና የውሃ ዳርቻዎች ውስጥ ንጹህ ውሃን ለማግኘት ሙከራ ሲያደርግ ነበር። በ 1970 ዎቹ በጸረ አፓርታይድ፣ ጸረ ኒውክሌር እና አዲስ አስተማማኝ የሃይል ንቅናቄዎች ውስጥ እንቅስቃሴ ያደርግ ነበር። በኩዋከር የሰላም ፈጣሪዎች ተነሳሽነት፣ በአዲስ ኢንግላንድ ውስጥ ካሉ የትስስር ቡድኖች ጋር በመለማመድ ሰላማዊ የህዝብ አመጽ ውስጥ አሰልጣኝ ሆነ። Running-Grass ሌሎች የአካባቢ

አስተማሪዎች እና የባህል ሰራተኞችን በመምራት ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት፣ Three Circles Center፣ ባለብዙ ባህል እና ማህበረሰቡን መሰረት ያደረገ የአካባቢ ትምህርት፣ የግንኙነት፣ እና የማህበረሰብ ተሳትፎ በመስራት አስተዋጽዖ ባበረከተበት ሳን ፍራንሲስኮ ወንዝ አካባቢ ለሶስት አስርት አመታት ኖሯል። በ 1991 በተደረገው First National People of Color Environmental Leadership Summit (የመጀመሪያው የሃገር አቀፍ ቀለም አካባቢ አመራር ጉባኤ) 300 ልኡካን ውስጥ አንዱ ነበር። በሁለት የ Environmental Protection Agency (EPA፣ የአካባቢ ጥበቃ ኤጀንሲ) ክልሎች የአካባቢ ፍትህ አስተባባሪ በመሆን ከ22 አመታት በኋላ ጡረታ ወጥቷል እናም በተለያዩ የመንግስት እርከኖች ያሉ የአካባቢ ፍትህ ጉዳዮችን በመለየት ለመፍታት እና የህብረተሰቡን ድምጽ በማጉላት ረገድ ልምድ አምጥተዋል። ከትምህርት ተቋማት እና ከመንግስት ኤጀንሲዎች ጋር በመመካከር እና በ Antioch University የ Urban Environmental Education (የከተማ አካባቢ ትምህርት) የምሩቅ ፕሮግራም ትምህርት ከፍተኛ መምህር በመሆን የ Three Circles ስራውን ቀጥሏል። Running Grass ከምስጋና ጋር በ Puget Sound ክልል፣ የስኳሚሽ ጎሳ የባህላዊ መሬት ይኖር፣ ያሳድግ እና ይወድ ነበር።

ስም፡- Rosalinda Guillen

መቀመጫ፡- የማህበረሰብ ተወካይ

የኢሜይል አድራሻ፡-

የስራ ዘመኑ የጀመረው፡- 01/06/2022

የስራ ዘመኑ የሚያበቃው፡- 07/25/2025

ግለ-ታሪክ፡- Rosalinda Guillen (እርሷ/የእርሷ)በ C2C ተዋረዳዊ ባልሆነው ኢኮፌሚኒስት አመራር ውስጥ Community to Community መስራች እና መሪ ስትራቴጂስት እና ባለራዕይ ናት። አመለካከቷ በመሰረታዊነት በብዙ-ዘር፣ የስራ-መደብ ማህበረሰብ ማደራጀት የ Rainbow Coalition ሞዴል፣ የ Cesar Chavez የቤት ስብሰባ ሞዴል፣ The World Social Forum፣ የብራዚል Landless Workers Movement (MST፣ የመሬት አልባ ሰራተኞች ንቅናቄ) እና በእርሻ ስራ በማደግ በማስተዋወቅ እና በ La Conner, WA የእርሻ ሰራተኛ ሆኖ በማደግ ላይ በነበራት ትውውቅ ተጽዕኖ አድሮበታል። Rosalinda በ WA ስቴት የተደራጁ የእርሻ ሰራተኞች እና በሳሊናስ CA የእንጆሪ ማሳዎች አሏት። በካሊፎርኒያ እና በዋሽንግተን ስቴት የህግ አውጪዎችን እና ቀጣይነት ያለው ፖሊሲ እና እንቅስቃሴ በኢሚግሬሽን ጉዳዮች፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ የሰራተኛ መብቶች፣ የንግድ ስምምነቶች፣ የኢኮፌሚኒዝም እና የምግብ ሉአላዊነት እንቅስቃሴን ወደ አንድነት ኢኮኖሚ በማጠናከር ላይ በሚደረጉ የፖሊስ እና የንቅናቄ ግንባታ ላይ ውይይቶችን በማሳደግ የእርሻ ሰራተኞችን ወክላለች።

ስም፡- Aurora Martin

መቀመጫ፡- የማህበረሰብ ተወካይ

የኢሜይል አድራሻ፡-

የስራ ዘመኑ የጀመረው፡- 01/06/2022

የስራ ዘመኑ የሚያበቃው፡- 07/25/2025

ግለ-ታሪክ፡-

ስም፡- David Mendoza

መቀመጫ፡- በሰፊ፣ ሹመቱ ተግባራዊ በሆነ እና በተመረመረ ስራ ላይ መሰረት ያደረገ እና በአካባቢያዊ ፍትህ ላይ ያተኮረ ተወካይ

የኢሜይል አድራሻ፡-

የስራ ዘመኑ የጀመረው፡- 01/06/2022

የስራ ዘመኑ የሚያበቃው፡- 07/25/2023

ግለ-ታሪክ፡-

ስም፡- የተከበሩ Sylvia Miller

መቀመጫ፡- የጎሳ ማህበረሰቦችን የሚወክል አባል

የኢሜይል አድራሻ፡-

የስራ ዘመኑ የጀመረው፡- 3/11/2022

የስራ ዘመኑ የሚያበቃው፡- 7/25/2024

ግለ-ታሪክ፡- Sylvia Miller ተወልዳ ያደገቺው በዋሽንግተን ውስጥ ነው። በ1977 ከ Stadium High School ተመርቃለች እናም ትምህርቷን በ Tacoma Community College እና Bates Technical College ቀጥላለች። Sylvia Miller ለህንዶች የፑያሉፕ ጎሳ እንደወጣት አስተባባሪ፣ የአሳ ንግድ ኢንዱስትሪ ጸሃፊ፣ የ Tribal Council (የጎሳ ምክር ቤት) ዋና ጸሃፊ፣ የ Job Training Partnership Act (JTPA፣ የስራ ስልጠና አጋርነት ህግ) ዳይሬክተር፣ የህግ አስፈጻሚ ላኪ፣ የአስተዳደር ረዳት በመሆን ሰርታለች። ቀደም ሲል በ Tribal Council ውስጥ ለሁለት የስራ ዘመን አገልግላለች።

ስም፡- Esther Min፣ PhD፣ MPH

መቀመጫ፡- የአካባቢ ፍትህ ባለሙያ ሆኖ የሚያገለግል የአካባቢ ፍትህ ባለሙያ ወይም የአካዳሚ ሰራተኛ

የኢሜይል አድራሻ፡-

የስራ ዘመኑ የጀመረው፡- 01/06/2022

የስራ ዘመኑ የሚያበቃው፡- 07/25/2023

ግለ-ታሪክ፡- Esther Min፣ PhD፣ MPH (እርሷ/የእርሷ) በዋሽንግተን ስቴት ውስጥ የአካባቢ ፍትህ ሰራተኛ ናት። ስራዋ በምርምር እና በህዝብ ጤና ልምምድ በማህበረሰብ-አካዳሚክ-መንግስት አጋርነት በኩል የአካባቢን እና የአየር ንብረት ፍትህ መርሆችን ማስተዋወቅ ላይ ያተኮረ ነው። በማህበረሰቡ የሚመሩ መሳሪያዎችን እና የማህበረሰቡን ምላሽ፣ ምርምር-ለ-ስራ ፕሮጀክቶችን፣ ማህበረሰብ የመስማት ክፍለጊዜዎች በማካሄድ እና በአካባቢ የጤና ጉዳዮች ላይ ለማህበረሰብ፣ ለአካዳሚክ እና ለመንግስት ኤጀንሲዎች የግንኙነት ምርቶችን በማሳደግ ላይ ልምድ አላት።

ስም፡- Todd Mitchell

መቀመጫ፡- በህንፃ እና በግንባታ ንግድ ውስጥ ሰራተኞችን የሚወክል የሰራተኛ ማህበር አባል ወይም ሃላፊ የሆነ ተወካይ

የኢሜይል አድራሻ፡-

የስራ ዘመኑ የጀመረው፡- 01/06/2022

የስራ ዘመኑ የሚያበቃው፡- 07/25/2023

ግለ-ታሪክ፡- Todd Mitchell ለ Heat & Frost Insulators and Allied Workers Local 7 የቢዝነስ ሃላፊ/የፋይናንስ ጸሃፊ ነው። ከ ጆ George Meany College of Labor የእውቅና ሰርትፍኬት አለው፣ እንዲሁም ከ HFIAW የማስተማር ሰርትፍኬቶችን አግኝቷል። በመላው ዩናይትድ ስቴትስ የውትድርና አገልግሎት አባላትን ወደ ኮንስትራክሽን ልምምድ ፕሮግራሞች በቀየረበት በ Washington State Helmets to Hardhats (የዋሽንግተን ስቴት ሄምሌትስ እና ሃርድሃትስ) ፕሮግራም የቀድሞ ዳይሬክተር ነው። Mitchell የቀድሞ ወታደሮችን በተሻለ መልኩ ለማገልገል የፌደራል፣ የክልል እና የአካባቢ መንግስታትን ከ Labor management Cooperative Trust ማሰልጠኛ ፕሮግራሞች ጋር በጋራ እንዲሄዱ በማድረጉ እውቅና ተሰጥቶታል። በስራ፣ Mitchell ለልምምድ እድገት፣ ክልላዊ አቀራረቦችን አድርጓል፣ ይህም የማጠናቀቂያ ደረጃዎች እንዲጨምሩ አድርጓል። የሳምንቱን መጨረሻ ቀናት ከ Cesky Fousek፣ Atli ጋር በተራሮች ወይም በሜዳዎች ውስጥ ሊገኝ ይችላል።

ስም፡- የተከበሩ Misty Napeahi

መቀመጫ፡- የጎሳ ማህበረሰቦችን የሚወክል አባል

የኢሜይል አድራሻ፡-

የስራ ዘመኑ የጀመረው፡- 02/11/2022

የስራ ዘመኑ የሚያበቃው፡- 07/25/2024

ግለ-ታሪክ፡- የምክር ቤት አባል Napeahi ስራዋን ለቱላሊፕ ጎሳዎች በትጋት ሰርታለች እናም በጎሳ መንግስት እና በካሲኖ ውስጥ የተለያዩ የስራ መደቦች ላይ ሰርታለች። በጎሳ መንግስት ሂደቶች እና ስርዐቶች ውስጥ ከሃያ ሶስት አመታት በላይ ልምድ አላት እናም ከ Columbia College በቢዝነስ አስተዳደር የመጀመሪያ ዲግሪዋን ይዛለች። ማህበረሰቧን ማገልገል እና ለሁሉም የጎሳ ዜጎች ፍትሃዊ የጥቅማ ጥቅሞች ስርጭት የሚያቀርቡ ፖሊሲዎችን መፍጠር ያስደስታታል። አሁን ላይ የሶንሆሚሽ ካውንቲ የ United Way የቦርድ አባል በመሆን ታገለግላለች። በትርፍ ጊዜዋ፣ Napeahi ከቤተሰቦቿ፣ ከባለቤቷ Jay እና ከሶስት ልጆቻቸው ጋር ጊዜ ማሳለፍ ያስደስታታል። ጉጉ አንባቢ ስትሆን ከውሾቿ፣ ከ Ivy እና Tito ጋር ጊዜ ማሳለፍ ያስደስታታል።

ስም፡- Nirae Petty

መቀመጫ፡- የወጣት ተወካይ

የኢሜይል አድራሻ፡-

የስራ ዘመኑ የጀመረው፡- 01/14/2022

የስራ ዘመኑ የሚያበቃው፡- 07/25/2023

ግለ-ታሪክ፡- Nirae Petty (እርሷ/የእርሷ) በሲያትል WA ተወልዳ ያደገች የኪንግ ካውንቲ ነዋሪ ናት። የጥቁር ተማሪዎች ህብረት ምክትል ፕሬዘዳንት እና የተማሪ አካል ፕሬዘዳንት በመሆን ባገለገለችበት፣ በ Rainier Beach High School የጠበቃ እና የፍትህ ፍላጎትን አሳድጋለች። በ Western New Mexico University ዋና ትምህርቷን በምትወስድበት ጊዜ፣ Nirae በአካባቢያዊ ዘረኝነት እና የአካባቢ ፍትህ (EJ) ስራ ታሪክ ላይ፣ በተለይም በመኖሪያ ቤት ላይ ትኩረት አድርጋለች።። በቅርቡ ከ Central Washington University በቅርቡ የተመረቀች፣ በህግ እና በፍትህ የመጀምሪያ ዲግሪዋን ባገኘችበት በሴንትራን ዋሽንግተን ዩኒቨርሲቲ በቅርቡ የተመረቀችው Nirae የአየር ንብረት ለውጥን ለመዋጋት እና የአካባቢ ጤና ልዩነቶችን በአካባቢያዊ እና በአለም አቀፍ ደረጃ ለመቀነስ ከፍተኛ ፍላጎት አላት። የ Urban League of Metropolitan Seattle (ULMS) የጠበቃ ፕሮግራም ስራ አስኪያጅ እንደመሆኗ፣ Nirae በአካባቢ ፍትህ ላይ ትኩረትን ለማካተት የ ULMS የህግ አውጪ ስራን ማስፋፋት እና ማህበረሰብ ከ EJ ስራ ጋር ያለውን ተሳትፎ ለመጨመር ከአካባቢዋ ኤጀንሲዎች እና ድርጅቶች ጋር መስራት ጀመረች። የአካባቢ ኢ-ፍትሃዊነትን ለመቅረፍ የመጀመሪያው እርምጃ ተጋላጭ የሆኑ ማህበረሰቦችን፣ በተለይም ወጣቶችን እና አዋቂዎችን በትምህርት እና በውክልና ማጎልበት ነው ብላ ታምናለች።

ስም፡- Faaluaina Pritchard

መቀመጫ፡- የማህበረሰብ ተወካይ

የኢሜይል አድራሻ፡-

የስራ ዘመኑ የጀመረው፡- 01/06/2022

የስራ ዘመኑ የሚያበቃው፡- 07/25/2025

ግለ-ታሪክ፡-

ስም፡- Raeshawna Ware

መቀመጫ፡- የማህበረሰብ ተወካይ

የኢሜይል አድራሻ፡-

የስራ ዘመኑ የጀመረው፡- 3/11/2022

የስራ ዘመኑ የሚያበቃው፡- 7/25/2025

ግለ-ታሪክ፡-

## ለምክር ቤቱ የኤጀንሲዎች ግንኙነቶች

David Bayne

ኤጀንሲ:- Washington Department of Health (የዋሺንግተን ግዛት ጤና መምሪያ)

ማዕረግ፦ የ Office of Strategic Partnerships (የስልታዊ አጋርነት ቢሮ) ምክትል ጸሃፊ

Laura Blackmore

ኤጀንሲ:- Puget Sound Partnership (የፐጌት ሳውንድ አጋርነት)

ማዕረግ፦ ዋና ዳይሬክተር

Tom Burgert

ኤጀንሲ:- Washington State Department of Natural Resources (የዋሽንግተን ስቴት የተፈጥሮ ሃብቶች ክፍል)

ማዕረግ፦ የሰራተኞች ምክትል ሃላፊ

Allison Dane Camden

ኤጀንሲ:- Washington State Department of Transportation (የዋሽንግተን ስቴት የመጓጓዣ ክፍል)

ማዕረግ፦ የ Multimodal Development and Delivery (የመልቲሞዳል እድገት እና አቅርቦት) ምክትል ረዳት ጸሃፊ

Michael Furze

ኤጀንሲ:- Washington State Department of Commerce (የዋሽንግተ ስቴት የንግድ መምሪያ)

ማዕረግ፦ ረዳት ዳይሬክተር፣ State Energy Office (የስቴት ኢነርጂ ቢሮ)

Nicole Johnson (ኒኮል ጆንሰን)

ኤጀንሲ:- Washington State Department of Agriculture (የዋሽንግተን ስቴት የግብርና መምሪያ)

ማዕረግ፦ የፍትሃዊነት ፖሊሲ አማካሪ

Millie Piazza

ኤጀንሲ:- Washington State Department of Ecology (የዋሽንግተን ስቴት የስነ ምህዳር መምሪያ)

ማዕረግ፦ የ Office of Equity & Environmental Justice (የፍትሃዊነት እና የአካባቢ ፍትህ ቢሮ) ስራ አስኪያጅ

# የአካባቢ ፍትህ ምክር ቤት ሰራተኛ

ስም፡- Theo Cielos (እነርሱ፣እርሷ)፣ MPP

የማህበረሰብ አገልግሎት አስተባባሪ

የኢሜይል አድራሻ፡-

ግለ-ታሪክ፡- በዝቅተኛ አገልግሎት ባለበት፣ በቀይ መስመር ላይ ባሉ ማህበረሰቦች መካከል መወለዱ እና በዘር እና በአካባቢያዊ ኢፍትሃዊነት ማደጉ Theo አሁን ያለውን ሁኔታ ለማፍረስ በሚታገለው የእያንዳንዱ እንቅስቃሴዎች ውስጥ እንዲሳተፍ አነሳስቶታል። በ የማይታለፉ የሚመስሉ የመዋቅር እንቅፋቶች ተስፋ መቁረጥ፣ እና በባህላዊ ቻናሎች መሻሻል አለመኖሩ Theo የማህበረሰቡን ውጤቶች የሚነኩ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች አካል የመሆን ፍላጎቱን አነሳስቶታል።

በ Seattle Centra የሶሺዮሎጂ ተጓዳኝ ዲግሪውን ካጠናቀቀ በኋላ፣ Theo በ Smith College የአካባቢ ሳይንስ ዲግሪ አግኝቷል። በመጨረሻው አመታቸው በስሚዝ፣ Theo በ UMass Amherst በመማር በህዝብ ፖሊሲ የሁለተኛ ዲግሪውን አግኝቷል። በአካባቢ ጉዳዮች ላይ ሳይንሳዊ መረዳትን ማግኘቱ እና በአካባቢ ልዩነቶች እና ፖሊሲዎች ላይ ተቋማዊ ሌንስ መኖሩ Theo እንደ የአካባቢ ፍትህ ባለሙያ ችሎታቸውን ለማስፋት እና ለመቅረጽ የሚያስችሉ መሳሪያዎችን አቅርቧል።

በታሪክ የተገለሉ ማህበረሰቦች አካል መሆኑ እና ከ *Jemez Principles* ጋር የማህበረሰብ አስተዳዳሪ ሆኖ መስራቱ Theo በአካባቢያዊ እና በአየር ንብረት ፖሊሲ ውስጥ ትርጉም ያለው የማህበረሰብ ድምጽ አለመኖሩን ማወቁ ተሰምቶታል። ከ Environmental Justice Counci (የአካባቢ ፍትህ ምክር ቤት) ጋር ለመስራት በጣም የተደሰቱት ንግግሮችን ወደ እውነታነት ለመቀየር እና ሁሉንም ሰው የሚጠቅሙ አዳዲስ ስርዓቶችን ለመፍጠር ስለምናግዝ ነው። Theo በባህላዊ የባህር ዳርቻ መሬት ሳሊሽ ህዝቦች፣ የአሁኑን እና ያለፍትን የዱዋሚሽ ህዝቦች ጨምሮ በሲያትል Central District ይኖራል።

ስም፡- Rowena Pineda (እርሷ/የእርሷ)፣ M.Ed።

ሚና፡- የአካባቢ ፍትህ አማካሪ

የኢሜይል አድራሻ፡-

ግለ-ታሪክ፡- በ 1981 Rowena አባቷ እና ወንድሟ አያቷ፣ አክስቶቿን፣ አጎቷን እና የአጎቶቿ ልጆች ለመቀላቀል ከፊሊፒንስ ወደ ሳን ፍራንሲስኮ ወንዝ አካባቢ ሄደዋል። የ6 እህቶች እና ወንድሞች ታላቅ እና የ 9 የእህት/የወንድ የሴት እና የወንድ ልጆች አክስት ነች። የ Rowena የአካባቢ ፍትህ የመጀመሪያ ስራዋ በ 1990 ዎቹ መጀመሪያ ላይ በኦክላንድ፣ CA ውስጥ ባሉ በ BIPOC ልጆች መካከል የሊድ መመረዝ ችግርን ለመቅረፍ የሚሰራ የማህበረሰብ አደራጅ ነበር። ባለፉት አመታት፣ ጥራት ያለው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ፕሮግራሞችን ማግኘትን እና Affordable Care Act (ተመጣጣኝ የእንክብካቤ ህግ) ን ማጽደቅን ጨምሮ በሌሎች ጉዳዮች ላይ ሰርታለች። በይበልጥ የሚታወሰው ማህበረሰብ የማደራጀት እንቅስቃሴ የ Rowena ስራ የግሏ ነበር። አባቷ በስህተት እንዲያቆም ከተደረገ በኋላ ወደ ስራው እንዲመለስ ማድረግን ያካትት ነበር።

Rowena በ 2005 ከራሷ ቤተሰቦች ጋር ወደ ስፖኬን ተዘዋወረች። ልጇ Ryan፣ ከ Lewis & Clark High School፣ ከ Whitworth University እና ከ Gonzaga University School of Law ተመራቂ ነው። የ Environmental Justice United Way የማህበረሰብ ትብብር እና ፍትሃዊነት ዳይሬክተር እና ከ 2010-2020 በ Spokane Regional Health District (ስፖኬን ክልላዊ የጤና ዲስሪክት) የፕሮግራም ስራ አስኪያጅ ነበረች። በአሁኑ ጊዜ በ APIC ስፖኬን እና በስፖኬን Council (የአካባቢ ፍትህ ምክር ቤት) ሰራተኞችን ከመቀላቀሏ አስቀድማ፣ Rowena ከ 2020-2021 በስፖኬን ካውንቲ YWCA የዳይሬክተሮች ቦርድ ውስጥ ትገኛለች። በ 2020 በ City of Spokane (ስፖኬን ከተማ) Lodging Tax Advisory Committee (ሎጅንግ የታክስ አማካሪ ኮሚቴ) ተሹማለች። Rowena የመጀመሪያ ዲግሪዋን ከ Brandeis University እና የሁለተኛ ዲግሪዋን ከ Holy Names University አግኝታለች።

ስም፡- Sierra Rotakhina (እርሷ/የእርሷ)፣ MPH

ሚና፡- Environmental Justice Council (የአካባቢ ፍትህ ምክር ቤት) ስራ አስኪያጅ

የኢሜይል አድራሻ፡-

ግለ-ታሪክ፡- Sierra Rotakhina ያደገችው ከድህነት፣ ከመርጃዎች እና ስራዎች እጦት፣ እና የውጪ ቱሪዝም ማስተዋወቅ ባሻገር የተራራው ኑሮ ውብ ሀብቶች ባሉባት የገጠር ከተማ ውስጥ ነው (የመቋቋም ችሎታ፣ ጠንካራ የማህበረሰብ ስሜት፣ ጎረቤቶችዎን የመንከባከብ ባህል፣ እና የአካባቢ ውበት) ባሉበት ትንሽ የገጠር ከተማ ውስጥ ነው። በገቢ፣ ጤና እና የሃብቶች ተደራሽነት ልዩነቶች ተከቦ ማደጉ ሴራ የሁለተኛ ዲግሪዋን በህዝብ ጤና እንድትማር እና ፍትሃዊነትን እና ፍትህን ከስቴት መንግስት ፖሊሲዎች ፣ ፕሮግራሞች፣ እና ጥናቶች ጋር ለማዋሃድ ስራዋን እንድሰራ አድርጓታል። ከ Environmental Justice Council አስቀድማ Sierra የ Washington State Board of Health (የዋሽንግተን ስቴት የጤና ቦርድ)፣ የ Interagency Council on Health Disparities (በጤና ልዩነቶች የገዥው መስተጋብር ምክር ቤት)፣ የ Washington State Supreme Court Gender and Justice Commission (የዋሽንግተን ስቴት ጠቅላይ ፍርድ ቤት የስርዓተ-ፆታ እና የፍትህ ኮሚሽን) እና በርካታ አማካሪ ኮሚቴዎችን ስራ ሰርታለች።

የስብሰባ ማስታወቂያ፡- Environmental Justice Council (የአካባቢ ፍትህ ምክር ቤት) ስብሰባ እያካሄደ ነው፣ እባክዎ በ [DATE] ይቀላቀሉን። በስብሰባዎች የቋንቋ ትርጉሞችን፣ የተተረጎሙ የስብሰባ ቁሳቁሶችን፣ ወይም ሌላ ማሻሻያዎችን ለመጠየቅ፣ እባክዎ በ envjustice@doh.wa.gov በማንኛውም ቋንቋ ኢሜይል ይላኩ ወይም በ 360-584-4398 ይደውሉ (የስልክ ትርጉም ማግኘትይችላሉ)።